# የሙስሊሙ ማህበረሰብ ሳንቲሞችን የማሰብሰብ የትግል ስልት:

## ወያኔን ማጠናከሪያ ወይስ ማዳከሚያ?

ዶ/ር ዘላለም ተክሉ

3/28/2015

ሰሞኑን በኢሳት ሬዲዮና ቴሌቪዝን ፕሮግራሞች በተደጋጋሚ እንደሳማሁት የሙስሊሙ ማህበረሰብ ላለፉት ሶስት ዓማታት ሲያካሂድ የነበረውን የተቃውሞ ትግል በአዳዲስ ፈጠራዊ ስልቶች በመታገዝ ማካሄድ መጀመሩን ተረድቻለሁ:: በዚሁም መሰረት ከሙቶ በላይ አዳዲስ ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀና ሰሞኑንም ሳንቲሞችን በመሰብሰብ ከገበያ እንዲወጡ የማድረግ ዘመቻ መጀመሩ ይፋ መሆኑንና ውጤትም እያስመዘገበ መሆኑን ኢሳት ከአዲስ አባባ ነዋሪዎች ጋር ባደረገው ቃለመጠይቅ እያረጋገጠልን ይገኛል::

እኔ በእውነቱ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ወያኔ የገፈፈውን የኃይማኖት ነጻነት ለማስመለስ የሚያደርገውን ትግል በከፍተኛ ደረጃ እደግፋለሁ:: ይህንን ዓላማቸውን ለማሳካት ሲሉ የአገት ለአንገት ትንቅንቅ የሚያደርጉትን፣ መላው ሙስሊም ወገናችንን በትጋት፣ በጀግንነትና በቆራጥነት እየመሩ ላሉትና በወያኔ ማሰቃያና ማሳቀቂያ እስር ቤቶች ለዓማታት በእስር ቢቶች ለሚማቅቁት ለነአቡበከር፣ አህመዲን ጀሚል፣ ሼክ ሱልጣን፣ ሼክ መከተና ሌሎችም ጭምር ትልቅ ከበሬታ አለኝ::

ይህንንም አምባገነንና ዘረኛ መንግስት በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚም ማዳከም እንደሚቻል ያሳዩት ብስለት፣ ምጥቀትና ጥንቅር መቼም ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል ተጓዳኝ ትግል ትልቅ ትምህርት ሰጪ ነው ብዬ አምናለሁ:: ቀጣይነቱና ተከታታይነቱ እንዲሁም ያመጣው ተጽዕኖ ባይታወቅም የቴሌኮሚኒኬሽንን የፋይናንስ አቅም ለማዳከም ታስቦ ላንድ ቀን ይሁን ለተወሰኑ ሰዓታት ሞባይ ቴሌፎኖችን በመዝጋት ( ባለመጠቀም) የተጀመራው አድማ በጣም ሊጠናከር የሚገባው የትግል ስልት ነው ብዬ በሙሉ ልብ አምናለሁ፣ ወደፊትም ለተገባራዊነቱ ተባብሬ ለመስራት ቃል እገባለሁ::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባለብኝ ተደራራቢ የግል ስራ ምክንያት ጊዜ በማጣት የሃገሬን ወቅታዊ ጉዳይ በተመለከተ ሳቀርብ የነበረውን ጽሁፍና አስተያየት ባቋርጥም፣ ይህንን "የሳንቲም ማሳባሰብ የትግል ስልት" ጉዳይ ስሰማ ባለችኝ የተጣበበ ትንሽ ጊዜ የሚከተለውን አስተያየት ለመስጠት ተገደድኩኝ::

ጉዳዩም እዲህ ነው::

ኢሳት ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ተወካዮችና ቃል አቀባዮች እንዳገኘውና እንደዘገበው፣ በአገሪቱ በጥቅም ላይ ያሉትን ሳንቲሞች ከገበያ በማውጣት ወያኔን በኢኮኖሚ ማዳከም እንደሚቻል ተገልጿል:: አሁን የተጀመረው ዘመቻም በታክሲዎችና በተለያዩ የገበያ ቦታዎች  የምንዛሪ እጥረት እየፈጠረ እንደሆነ የተዘገበ ሲሆን ይህ ዘመቻ በስፋት ከቀጠለም የዋጋ ግሽበትን (Inflation) ሊያስከትል እንደሚችልና ይህም የኢኮኖሚ ቀውስ መንግስትን እንደሚያስጨንቀውና ምናልባትም አዝማምያውን ከፈራው የሙስሊሙን ህብረተሰብ ጥያቄዎች የመመለስ ግዴታ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ተገምቷል::

ይህ ስልት ከአጭር ጊዜ ግብ ማለትም ምንዛሪ ከማሳጣት አንጻር ትንሽ መጨናነቅ ሊያስከት ይችላል ብዬ እገምታለሁ። ነገር ግን ከኢኮኖሚያዊ መላም ምት（macoreconomic theory）ትንታኔ አንጻር ሲታይ ግን ገንዘብን （ሳንቲሞችንም ጨምሮ） ከገበያ ማውጣት የዋጋ ግሽበትን (Inflation) ማባባሻ ሳይሆን የማዳከሚያ ብሎም ማቆሚያ ዋነኛ ስልቶች

አንዱና መሆኑ ለመግለጽ እወዳለሁ ፡ ፡ እያወራን ያለነው ብዙ ብዙ ሳንቲሞች ማሰባሰብና ከገበያ ማውጣትን ነው ፡ ፡ እነዚህ ሚሊዮን ሳንቲሞች ደግሞ ሚሊዮን ብሮች ይሆናሉና፣ ሚሊዮን ብሮች ከገበያ ወጡ ማለት ነው ፡ ፡

እንግዲህ አስቡት፣ በመጀመሪያም በኢትዮጵያ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበቱ (Inflation) የተከሰተው ከ 1995 ምርጫ ወዲህ ወያኔ የህዝቡን ትግልና ነጻ ፕሬስን ለዳከም፣ ህዝቡን ለማፈን የሚረዳውን የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ሀይሉን ለማጠናከር ብዙ ገንዘብ ያስፈልገው ነበርና ምጫውን በማጭበርበሩና ሰላማዊ ወገኖችን በጠራራ ፀሃይ በመጨፍጨፉ ምክንያት የውጭ ዕርዳታ ቆሞበት ( ወይም ቀንሶበት) ስለነበረ ፣ የወረቀት ገንዘብ ማተም (Printing money) ግዴታው ነበርና አደረገው ፡ ፡ ያ የወረቀት ገንዘብ በቂ ምርት በሌለበት ሃገር ገበያ ውስጥ በብዛት ሲገባ ውጤቱ የዋጋ ግሽበት (Inflation) ነበር ፡ ፡ ከዛም በኋላ በ ዓለም አቀፍ አሸባሪን የመዋጋት ስበብ ከታላላቅ የአለም መንግስታት፣ የ ዓለም ባንክና (World Bank) የገንዘብ ድርጅቶች (IMF) ከፍተኛ ገንዘብና የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ቻለ፣ ያም የዋጋ ግሽበቱን (Inflation) አባባሳው ፡ ፡ ይህንን የተባባሰ የዋጋ ግሽበትን (Inflation) ለማብረድና ለማቆም ሁሉም የኢኮኖሚ ባለሙያዎችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ወያኔን እየመከሩት ያለው፣ በትርፍነት በገበያ የተዘራን ገንዘብ (excess money supply) እንዲሰበስብ ነው ፡ ፡ የሃገር ውጥ ምርት እንዲያድግ ማድረግም ሌላው ዋና መፍትሄ ነው ፡ ፡

የዋጋ ግሽበቱ (Inflation) ማስታገሻና ማቆሚያው ሳይንሳዊ መፍትሄ ከላይ የተጠቀሰው መንገድ ቢሆንም ወያኔ ያን አካሄድ እስካሁን ተግባራዊ ሊያደርገው አልቻለም ፡ ፡ ታዲያ ይሄ በሙስሊሙ ማህበረሰብ የተጀመረው “የሳንቲም ማሰባሰቡ ዘመቻ” ወያኔ ሊያደርግ ያቃተውን ወይም ያልፈለገውን የመፍትሄ እርምጃ ተገባራዊ ማድረግ ይሆናል ብሎ መገመት አይቻልን? ይሄ ግምቴ እውን ከሆነም ወያኔን በኢኮኖሚ ማዳከም ሳይሆን ማጠናከር ነው ብሎ መደምደምስ አይቻልምን ? ምክንያቱም ወያኔ ለአሥር ዓመታት ሊፈታ ያልቻለውን የኑሮ ውድነት ችግር የሙስሊሙ ህብረተሰብ በፈቃደኝነትና በየዋህነት ሊፈታለት ነውና ፡ ፡

ታዲያ መፍትሄው ምንድነው ተብዬ ብጠየቅ ከሙያዬ አንጻር የሚከተለውን ሃሳብ በማቅረብ ጽሁፌን አጠቃልላለሁ ፡

ወያኔን በኢኮኖሚ ማስጨነቅ ከተፈለገ ሰመ ገናናው እንግሊዛዊው ኢኮኖሚስት ጆን ሚይናርድ ኬይንስ “The Paradox of Thrift” ብሎ የሰየመውን ኢኮኖሚያዊ ክስተት ተግባሪያዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ ፡ ፡ የዚህን ክስተት ትንታኔ ቀጥተኛ እንግሊዝኛ ቅጂ እጠቅሳለሁ ፡

John Maynard Keynes argued that if many households decide at the same time to increase their saving and reduce their spending, they may make themselves worse off by causing aggregate expenditure to fall, thereby pushing the economy into a recession[i].

ትርጓሜውም እያንዳንዱ ቤተሰብ ባንድ ላይና ባንድ ጊዜ በእጁ ያለውን ገንዘብ ቁሳቁሶችን ከመግዛት ይልቅ በአብዛኛው ቢቆጥበው አጠቃላይ የሃገሪቱን ወጪ ወይም አጠቃላይ ኢኮኖሚውን （GDP）በመቀነስ ራሱን ሊጎዳ ይችላል ብሎም የኢኮኖሚ ቀውስ ሊያመጣ ይችላል ማለት ነው ፡ በነገራችን ላይ ይህ መላ ምትና ክስተት እስካሁን በአሜሪካና በአውሮፓ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንታኔና ተግባሪዊ ዕቅዶች ውስጥ በታሳቢነት ይካተታል ፡ ፡

እንዴት ኢትዮጲያዊ ሆኖ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚያዳክም ሻጥር እንዲሰራ ምክር ይለገሳል ብለው የሚሟገቱ ወገኖች ሊኖሩ እንደሚችሉ እገ ምታለሁ ፡ ፡ እውነታም ያዘለ ሊመስል ይችላል ፡ ፡ ነገረ ግን ይሄንን የኢትዮጵያ ክፉ ደዊ

ለመንቀል እስካስቻለ ድረስ እያንዳዳንዱ ህዝቡ ትንሽም ቢሆን መስወዕትነትና መከራ ከፍሎም ለስኬቱ መተባበር ግዴታው ነው ብዬ እከራከራለሁ : :

እነሱስ ቢሆኑ ከደደቢት አራት ኪሎ እስኪደርሱ ስንትና ስንት ድልድይ አፍርሰው የለ፣ ስንትና ስንት ሚሊዮን ብር ገንዘብ ከኢትዮጲያ ባንኮች ዘርፈው የለ፣ እስካሁንም ለሃገሪቷ አልመለሱም አይደለ፣ ወደባችንንና ለም መሬቶቻችን ለባእዳና አሳልፈው ሰጥተውም አይደለ : :

አገራችን ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር : :

---

[i] Hubbard, R. G. and P. O’Brien, (2015), Macroeconomics, Fifth edition, New Jersey, NJ, Pearson Education. Inc. pp 401.